# ቃልህ፤ተፈጸመ፣(ከአዳነ መኮነን)

**“እግዚአብሔር፡አብራምንም፡እንዲአለው፡-ዘርህ፡ለእርሱ፡ባልሆነች፡ምድር፡ስደተኞች፡እንዲሆኑ፡በእርግጥ፡እወቅ፤ ባሪያዎች፡አድርገውም፡አራት፡መቶ፡ዓመት፡ያስጨንቋቸዋል።ደግሞም፡በባርነት፡በሚገዙአቸው፡ሕዝብ፡ላይ፡እኔ እፈርዳለሁ፤ከዚያም፡በኋላ፡በብዙ፡ከብት፡ይወጣሉ።አንተ፡ግን፡ወደ፡አባቶችህ፡በሰላም፡ትሄዳለህ፡በመልካም፡ሽም ግልና፡ትቀበራለህ።በአራተኛው፡ትውልድ፡ግን፡ወደዚህ፡ይመለሳሉ፡የአሞራውያን፡ኃጢአት፡ገና፡አልተፈጸመምና” ። (ኦሪት፡ ዘፍጥረት፡ምዕራፍ፡15።)**

ለአብራሃም የነገርከው፤ ቃልህ ተፈጸመ፤
ዘሩ ተሰብስቦ ጓዙን ጠቀለለ፤
ቀይ ባሕርን ተሻግሮ፤ተጓዘ ተመመ፤
የመከራው ዘመን አለቀ አከተመ፤
ከተስፋይቱ ምድር እስራኤል ከተመ።
　　አራት መቶ ዓመታት፤ የኀዘን ትካዜው
　　ቃልህ ደረሰና፤ተፈጸመ በአንድ ጊዜው።
የስደቱን ዘመን ፤ስቃይ የበዛበት
አምላክ አስወገደው፤ በሙሴ አማካይነት።
　　የራሄል እንባ፤ ሲደርስ ከሰማይ፤
　　የራሄል ጩሆት፤ ሲደርስ ከሰማይ፤
　　አምላክ ፍርዱን ሰጠ በቀይ ባሕር ላይ፤
　　ፈርዖንን አረገ፤ እስከ ሰራዊቱ ከዓለም እንዲለይ።
ትንቢቱ ተፈጸመ፤ ለአብርሃም የነገርከው፣
ከግብጽ ምድር እስራኤልን አወጣሃው፣
ከባርነት ቀንበር አላቀህ መለስከው።
　　ከሰማያት ወርደህ፤ ስታድን ታይተህ፣
　　ከፍጥረትህ ሁሉ፤ እስራኤልን መርጠህ፣
　　በተአምር ስታሻግር፤ ቀይ ባሕርን ከፍለህ፣
　　ታወቀ በአሕዛብ፤ ፈጣሪ መሆንህ።
በደረቁ መሬት እስራኤልን አሻግረህ፤
እስከ ሰራዊቱ ፈርዖንን አሰጠምህ፤
የከፈልከውን ውሃ አዙረህ መልሰህ።
　　እስራኤል ዘመረ ተሞልቶ በደሳታ፤
　　ለአብርሃም አምላክ ለኃያሉ ጌታ።
በደስታ ተጓዘ በሰላም ኀዳና
ሌሊት በብርሃን ቀንም በደመና
ረሃብ ሳያገኘው እየበላ መና ።
　　እስራኤል ጠገበ በሰማዩ እንጀራ፤
　　አንተ ተቀምጠህ በሲና ተራራ።
ጠጥቶም እረካ ከዐለት ከተገኘው፤
ሰው ያልደከመበት አንተ ባፈለቅኸው።
　　እኛም እንጠብቅ በምነታችን ጸንተን
　　በመስቀል ላይ ሆኖ በደሙ የዋጃትን
　　በቃሉ መሰረት እንዲባርክ ኢትዮጵያን።
ያባቶችን መንገድ እኛ ከሄድነበት
ተሎ ይፈጽማል በቃሉ መሰረት
እሱም ያዘንባል ማር እና ወተት
ጠግበን እንድንበላ ከምሳ እስከ እራት።
　　ልክ እንደ እስራኤል እኛንም አድነን፣
　　የትንቢቱ ቃልህ ተሎ ይድረስልን።

እንዲህ እንደከፋን እንደተሰቃየን
የሰላም እንጀራ ሳንበላ አንድ ቀን
እንዳንሰናበት ይችን ዓለም ትተን።
ፈውሱን ላክልን ይድረቅ ቁስላችን
የአንተ መድኃኒት ነው እኛን የሚያድነን
ለረጅም ዓመታት ይዞ ያሰቃየን
ቁስላችንን አድርቀው በሽታው ይልቀቀን።
ባገራችንም ሆነ በውጭም ተቀምጠን
ካለአንተ በስተቀር ማንም አይደግፈን
የሰው ልጅ እንደሆን ገፍቶ ነው የጣለን
ተርበን ተጠምተን አምላክ ያውቃል ስላልን።
ተሎ ይድረስልን የትንቢቱ ቃልህ፣
ከማለቁ በፊት በሙሉ ፍጥረትህ፤
ከስደት መልሰን ሀገር ሰላም አድርገህ።
ይዋል ይደር እንጂ ቃሉ መቼ ያልፋል፤
ለአብርሃም የነገረው ሲፈጸም አይተናል።
የነገሩትን ፤ የማይረሳ
የለመኑትን ፤ ይማይነሳ
እግዚአብሔር ብቻ ነው ለጋስ የማይሳሳ።
እኛም እንገረው ጸንተን በሃይማኖት
እንዲያስወግድልን ረሃብና ስደት
ደግሞም እንዲያበቃን ለሀገራችን መሬት
በዚህው እንዳንቀር አፈር ከሌለበት።
እንኳንስ ለሞተ በሕይወት ለአለም
ለስደተኛ ሰው ክብር አይሰጥም።
ከረሃብ ከበሽታ ከችግር አላቆ፤
ኢትዮጵያን ሲባርካት ከዓለም አልቆ፤
እግዜር ያሳየናል በኀብት አጥለቅልቆ።
ያዘንብላታል ማርና ወተትን፤
እንግዲህ አታይም የሰው ፊትና እጅን፤
ያድናታል እሱ ቁማ ከመለመን።

አቤቱ አምላክ ፈጣሪያችን ኢትዮጵያን አስባት ልጆቿ በገዛ ሀገራቸውና በስደት የሚደርስባቸውን ግፍና መከራ ድብደባና እስራት ሙቶ በጥርጊያ ላይ ወድቆ መታየት አንተም እንደ ሰው ይህን እያየህ አጨቅንባት ቃል በገባሃው መሰረት ተሎ ምህረት አውርድላት ፊትህንም ወደ እሷ መልስ እያልን ወደ አንተ እንጮሃልን።

በአሁኑ ሰዓት በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ዓለም የሚያደርሰውን ግፍና በደል እያየህ ዝም አትበል። ኢትዮጵያ ሀገራችን ለኛ ሲኦል ለአሕዛቦች ግን ገነት ሁናለች። ቃል በገባህው መሰረት እስራኤላውያንን ከስደት እንደመለስክ ሁሉ በእኛም በሕዝብህ ላይ ቀንበር የጫኑትን ልቦና ሰጥተህ ወይም ከቦታቸው አንስተህ ማርና ወተት ይፍሰስብሽ ብለህ የባረካትንና የቀደስካትን ሀገር ለኛ ለልጆቿ መልሰህ እንድታወርሰን ኃያሉ ስምህን እየጠራን ሌት ተቀን በጸሎት እንለምንህ አለን አሜን። ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!